መልእክት ዘጠኝ

## አማኞች በውስጥ የሚያድረውን ክርስቶስ በውስጥ በመለማመዳቸው መሠረት በመንፈሳዊ ገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ ሂደት በኩል እንደ የክርስቶስ አካል የቤተ ክርስቲያን ሕይወታዊ ግንባታ

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፦ 2 ሳሙ. 7፥12-14፤ ኤፌ. 3፥16-21

**I. ሁለተኛ ሳሙኤል 7፥12-14 መላው ማንነታችን በክርስቶስ እንደገና ይቀናበር ዘንድ እግዚአብሔር ወደ ውስጠ-መሠረታዊ ቅንብራችን ውስጥ ክርስቶስን ሊገነባ እንደሚያስፈልገን በማሳየት በምሳሌ በኩል የትንቢት መገለጥ ነው—ማቴ. 16፥18፦**

ሀ. በልቡ መሻት መሠረት የሆነው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ኢኮኖሚ ራሱን ወደ ሰው ውስጥ መገንባት እና ሰውን ወደ ራሱ ውስጥ መገንባት ነው (ኤፌ. 3፥16-17)፤ ይህ የጋራ መኖሪያ በአዲሲቱ ኢየሩሳሌም የሚጠናቀቀው የክርስቶስ አካል እውነታ ነው (ዮሐ. 15፥4-5፤ 1 ዮሐ. 2፥27-28፤ 3፥24፤ 4፥13፣ 15-16፤ ራእ. 21፥3፣ 22)።

ለ. እግዚአብሔር በኢኮኖሚው ያለው ውጥን ራሱን በክርስቶስ ወደ ማንነታችን ውስጥ መገንባት ነው—2 ሳሙ. 7፥12-14፤ ኤፌ. 3፥17፤ ዮሐ. 14፥20፤ ገላ. 4፥19፦

1. እግዚአብሔር ራሱን በክርስቶስ ወደ ውስጣችን መሥራት ይፈልጋል፤ ክርስቶስ የሆነው ነገር ሁሉ እና ክርስቶስ የፈጸመው ነገር ሁሉ ለዚህ አንድ ነገር ናቸው—ፊልጵ. 2፥13፤ ኤፌ. 3፥17፤ ቆላ. 3፥10-11።
2. እግዚአብሔር ራሱን በክርስቶስ ወደ ውስጣችን እንደ ሕይወታችን፣ ባህሪያችን እና ማንነታችን በመሥራት ራሱን በክርስቶስ ወደ ስብዕናችን ውስጥ እንዲገነባ ያስፈልገናል—ኤፌ. 3፥17።

**II. ኤፌሶን 3፥16-21 ሦስታንዱ አምላክ በራሱ እንደ ንጥረ-ነገር እና ከእኛም የሆነን ነገር እንደ ግንባታ ግብዓት የግንባታ ሥራ ለመሥራት ወደ ውስጣችን እንደመጣ ይገልጣል፤ ይህ በማቴዎስ 13 ባለው በዘሪው ምሳሌ ተገልጧል፦**

ሀ. ጌታ እንደ የሕይወት ዘር ወደ ሰዎች ልብ፣ ወደ ምድሩ ውስጥ ራሱን ይዘራል፣ ይህም በውስጣቸው ያድግ እና ይኖር እና ከውስጣው ይገለጥ ዘንድ ነው—ቁ. 3።

ለ. ዘሩ ወደ ምድሩ ውስጥ የተዘራው በምድሩ ውስጥ ባሉ ንጥረ-ነገሮች በመመገብ እንዲያድግ ነው፤ በውጤቱም፣ ፍሬው ከዘሩ እና ከምድሩ የወጡ ንጥረ-ነገሮች ውቅር ነው—ቁ. 23።

ሐ. እግዚአብሔር ወደ ውስጣችን ለመምጣቱ እና በውስጣችን ለማደጉ በውስጣችን በእግዚአብሔር የተፈጠሩ የተወሰኑ የሚመግቡ ንጥረ-ነገሮች አሉን፤ መለኮታዊው ዘር በውስጣችን ለማደጉ እግዚአብሔር የሰውን መንፈስ በሰው ውስጥ ካሉ ከሚመግቡ ንጥረ ነገሮች ጋር የሰው ልብን እንደ ምድሩ ጨምሮ ፈጥሯል—1 ዮሐ. 3፥9፤ 1 ጴጥ. 1፥23፤ ቆላ. 2፥19፦

1. በሕይወት የምናድግበት መጠን የሚመረኮዘው በመለኮታዊው ዘር ሳይሆን ለዚህ ዘር በምንሰጠው የሚመግቡ ንጥረ-ነገሮች ላይ ነው፤ የበለጠ የሚመግብ ንጥረ-ነገሮች ባቀረብን መጠን፣ ዘሩ ይበልጥ በፍጥነት ያድጋል፣ የበለጠ ያብባል—መዝ. 78፥8፤ ማቴ. 5፥3፣ 8፦
   ሀ. በነፍሳችን፣ በተፈጥሮአዊው ሰዋችን ከቆየን፣ መለኮታዊውን ዘር የሚመግቡ ምንም አይነት ንጥረ-ነገሮች አይኖሩም፤ ነገር ግን ወደ ውስጠ-ሰውነታችን ከጠነከርን እና ለመንፈሳችን ትኩረት ከሰጠን እና መንፈሳችንን ካንቀሳቀስን፣ የሚመግቡት ንጥረ-ነገሮች አቅርቦት ይሆኑለታል፣ ክርስቶስም ቤቱን በልባችን ውስጥ ይሠራል—ኤፌ. 3፥16-17፤ ሮሜ 8፥6፤ 1 ጢሞ. 4፥7።
   ለ. ጌታ ድሰታችን ለመሆን እንደ የሕይወት ዘር በውስጣችን እንዲያድግ ከፈለግን፣ ልባችንን ጥልቅ-ዝርዝር በሆነ ሁኔታ ለማስተካከል ሙሉ በሙሉ ለጌታ መከፈት እና ከእርሱ ጋር መተባበር አለብን—ማቴ. 13፥3-9፣ 19-23።
2. በአንድ በኩል፣ እግዚአብሔር እንደ ንጥረ-ነገር በራሱ ያጠነክረናል፣ በሌላ በኩል ደግሞ፣ እኛ ንጥረ-ነገሮቹን እንሰጣለን፤ በእነዚህ በሁለቱ እግዚአብሔር በክርስቶስ ውስጠ-መሠረታዊ ግንባታውን—የቤቱን ግንባታ—በመላው ማንነታችን ውስጥ ያከናውናል።

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ መሠረት፣ እድገት ከግንባታ ጋር እኩል ነው፤ ጌታ ኢየሱስ “ቤተ ክርስቲያኔን እሠራለሁ” ብሎ አወጀ (ማቴ. 16፥18)፤ ይህ ግንባታ የሚከናወነው በውስጣችን ባለው የመለኮታዊ ዘር እድገት ነው (1 ዮሐ. 3፥9፤ ኤፌ. 4፥15-16፤ ቆላ. 2፥19፤ ኤፌ. 2፥21-22፤ 1 ቆሮ. 3፥1፣ 6-9፣ 12፤ 16፥13)።

ሠ. የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ ራሱን ወደ ውስጣችን መሥራት ነው፣ ይህም በተፈጥሮአዊ ሕይወታችን ቀስ በቀስ የሆነ እና ውስጠ-መሠረታዊ የገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ ለውጥ የሆነውን መለወጥን የሚያመጣውን የመንፈሳዊ መብላላትን እና

መዋሐድን ገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ ሂደት እንለማመድ ዘንድ ነው፤ ይህ አዲሰቱ ኢየሩሳሌምን ለማጠናቀቅ ለክርስቶስ አካል መገንባት ነው—2 ቆሮ. 3፥18፦

1. የእግዚአብሔር ግንባታ እንዲከናወን፣ ሕይወት-የሚሰጥ መንፈስ የሆነውን ሕይወታዊውን፣ እስትንፋሳዊውን ክርስቶስ እንደ መንፈሳዊ ምግባችን፣ መጠጣችን እና እስትንፋሳችን መቀበል፣ ማብላላት እና ማዋሐድ ያስፈልገናል—ዮሐ. 6፥51፣ 57፤ 7፥37-39፤ 20-22።
2. ክርስቶስን በመብላት፣ በመጠጣት እና በመተንፈስ ስንደሰተው፣ የገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ ሂደት፣ መንፈሳዊ መፈጨት እና ገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ፣ በውስጣችን ይከናወናል፣ ክርስቶስም በውስጣችን ይሠራል፤ ይህ ውስጣዊ ገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ ልውጠት ነው፣ ልውጠት ደግሞ ግንባታ ነው—ሮሜ 12፥2፤ ፊልጵ. 1፥20-21፤ ተዛ. ራእ. 21፥18፤ 4፥3።

ረ. በመንፈሳዊ ገንባ-አፍራሽ ቅንባሮ ሂደት በኩል እንደ የክርስቶስ አካል የቤተ ክርስቲያን ሕይወታዊ ግንባታ በእውነቱ ያህዌ ለዳዊት በምሳሌያዊ መንገድ በ 2ኛ ሳሙኤል 7፥12-14 የተነበየው ነው።

**III. ለቤተ ክርስቲያን እንደ የክርስቶስ አካል መገንባት አማኞች በውስጥ የሚያድረውን ክርስቶስ በውስጥ መለማመዳቸውን በተመለከተ ጳውሎስ በኤፌሶን 3፥16-21 ጸለየ—4፥12፣ 16፤ 2፥21-22፦**

ሀ. ክርስቶስ በልባችን ውስጥ ቤቱን መሥራት ይችል ዘንድ ከዚያም የተነሣ መላው የውስጥ ማንነታችንን በራሱ እንዲያዝ፣ እንዲወርስ፣ እንዲሠረጽ፣ እና እንዲሞላ በመንፈሱ ወደ ውስጥ ሰውነታችን እንጠነክር ዘንድ ጳውሎስ ወደ አብ ጸለየ—3፥16-17።

ለ. ሦስታንዱ አምላክ ጳውሎስ አንቀሳቃሹ በሆነ በትልቅ ማሽን ሊመሰል ይችላል፤ አንድ ትምህርት መማር አለብን፣ ያም፣ በአጽናፍ-ዓለም ውስጥ ታላቅ መርህ አለ፤ ይህ መርህ እግዚአብሔር የሆነ ነገር ማድረግ መፈለጉ፣ ነገር ግን እርሱ “ማሽኑ” ብቻ እንደሚሆን እና የሆነ ሰው አንቀሳቃሹ እንዲሆን እንደሚያስፈልገው ነው፦

1. ጳውሎስ በኤፌሶን 3፥16-21 ያለውን ጸሎት ሲጸልይ፣ የመላው የክርስቶስ አካል ወኪል ነበር።
2. አብ፣ ወልድ እና መንፈስ የዚህ አጽናፍ-ዓለማዊ “ማሽን” ሦስት “ክፍሎች” ናቸው፣ አካሉ ደግሞ አንቀሳቃሹ ነው፤ ይህን ጸሎት አንቀሳቃሹን በመሆን ስንጸልይ፣ ግቡ፣ አላማው፣ ወልድ በልባችን ክፍሎች ሁሉ ውስጥ ቤቱን ይሠራ ዘንድ እያንዳንዱን የውስጥ ማንነታችንን ክፍል ወደ ውስጡ ሰውነታችን ለማጠንከር አብ ማስተላለፊያ በሆነው በመንፈሱ ይሠራል።

ሐ. ወደ ውስጡ ሰውነታችን በኃይል መጠንከር ያስፈልገናል ማለት የሚያመለክተው በውስጡ ሰው እንዳይደለን እና አብዛኛውን ጊዜ የምንኖረው በውጪው ሰው መሆኑን ነው—ቁ. 16፤ 1፥19-22፤ 3፥20።

መ. ክርስቶስ የልባችንን እያንዳንዱን ክፍል ለመያዝ መሻት አለው፦

1. *ቤቱን እንዲሠራ* የሚለው ሐረግ በግሪኩ አንድ ቃል ብቻ ነው፣ *ካቶይኬዖ*፡ መሠረታዊ በሆነ መልኩ ትርጓሜውም በመኖሪያ ስፍራ ተደላድሎ መኖር፣ መኖሪያ ስፍራ ማድረግ ማለት ሲሆን የዚህም ቃል ቅድመ ቅጥያ *ካታ* “ውስጣዊ” ማለት ነው—ቁ. 17።
2. ክርስቶስ በልባችን ጥልቀት ቤቱን ሲሠራ፣ ለእግዚአብሔር እርሻ በፍቅር ሥር እየሰደድን እና ለእግዚአብሔር ግንባታ በፍቅር እየተመሠረትን ነው—ቁ. 17።
3. ቤቱን በልባችን ሲሠራ ከቅዱሳን ሁሉ ጋር ልኬቱ የአጽናፍ-ዓለም ልኬት የሆነውን የማይለካውን ክርስቶስ ለማወቅ እንበረታለን—ቁ. 18፦
   ሀ. በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የክርስቶስ ልምምዳችን ሦስት-ደርዝ ያለው፣ እንደ ኩብ (ስፋቱ፣ ርዝመቱ፣ ከፍታው እና ጥልቅነቱ) መሆን አለበት፣ አንድ-ደርዝ ያለው፣ እንደ መስመር መሆን የለበትም።
   ለ. በማደሪያ ድንኳኑም በመቅደሱም፣ ቅድስተ ቅዱሳኑ ኩብ ነበር—ዘጸ. 26፥2-8፤ 1 ነገ. 6፥203
   ሐ. በመጨረሻ፣ አዲሲቱ ኢየሩሳሌም፣ የእግዚአብሔር ግንባታ፣ ዘላለማዊ ኩብ፣ ቅድስተ ቅዱሳን፣ አሥራ ሁለት ሺህ ምዕራፍ በሦስት ደርዝ ትሆናለች—ራእ. 21፥16።
4. ክርስቶስ ቤቱን በልባችን መሥራቱ ብዙዎች ለተካተቱበት መገለጡ፣ ለመክበሩ በሦስታንዱ አምላክ ሙላት እንሞላ ዘንድ ከመታወቅ የሚያልፈውን የክርስቶስን ፍቅር እንድናውቅ ያደርገናል—ኤፌ. 3፥19-21፤ ተዛ. ዘፍ. 24፥47፣ 53፣ 61-67።

ሠ. ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን የሚገነባው ራሱን ወደ ውስጣችን በመገንባት፣ ማለትም፣ ወደ መንፈሳችን ውስጥ በመግባት እና መላው ማንነታችንን ለመያዝ ራሱን ከመንፈሳችን ወደ አእምሮአችን፣ ስሜታችን እና ፈቃዳችን ራሱን በማሰራጨት ነው—2 ጢሞ. 4፥22፤ 1 ቆሮ. 6፥17፤ ኤፌ. 3፥17፦

1. ልባችን የውስጥ ክፍሎቻችን ጥቅል-ድምር፣ የውስጥ ማንነታችን ማዕከል እና ከዝንባሌ፣ ከፍቅር፣ ከደስታ፣ እና ከመሻት አንጻር ወኪላችን ስለሆነ፣ መላው የውስጥ ማንነታችንን ይቆጣጠራል፤ ለእያንዳንዱ የውስጥ ክፍልም አቅርቦት ይሰጣል፣ ያጠነክረዋልም።
2. ክርስቶስ ይበልጥ በውስጣችን ሲሰራጭ፣ የውስጥ ማንነታችንን እያንዳንዱን ክፍል በመያዝ እና እነርሱን በራሱ የራሱ በማድረግ ይበልጥ በውስጣችን ተደላድሎ ይቀመጣል፣ ቤቱንም በልባችን ይሠራል።
3. የቤተ ክርስቲያንን ግንባታ በተመለከተ በማቴዎስ 16፡18 ያለው የክርስቶስ ቃል እንዲፈጸም፣ ክርስቶስ መላው የውስጥ ማንነታቸውን በመውረስ፣ በመያዝ እና በመሙላት ቤቱን በልባቸው ጥልቀት እንዲሠራ ቅዱሳን ወደሚፈቅዱበት ሁኔታ ውስጥ ቤተ ክርስቲያን መግባት አለባት።
4. ክርስቶስ የውስጥ ማንነታቸውን ይበልጥ ሲይዝ፣ በአካሉ ውስጥ ከሌሎች ጋር ይበልጥ መገንባት የምንችል እንሆናለን—ኤፌ. 2፡21-22፤ 4፡12፣ 16።
5. ኤፌሶን 3፡17 በፍቅር ሥር ስለመስደድ እና ስለመመሥረት ይናገራል፤ ሥር መስደዳችን ማደግ የሚያስፈልጋቸው ተክሎች እንደሆንን ያመለክታል፣ መመሥረታችን ደግሞ መገንባት ያስፈልገናል ማለት ነው።
6. በቁጥር 18 መሠረት፣ በመጨረሻ በየግላችን በራሳችን ሳይሆን "ከቅዱሳን ሁሉ ጋር"፣ ማለትም፣ በአንድ ላይ እና በጋራ የክርስቶስን አጽናፍ-ዓለማዊ ልኬቶች—ስፋቱን፣ ርዝመቱን፣ ከፍታውን እና ጥልቅነቱን—ለማወቅ እንበረታለን፤ ይህ አንድ ላይ መገንባት እንደሚያስፈልገን ይገልጣል።
7. ክርስቶስ በልባችን ቤቱን ሲሠራ፣ እስከ እግዚአብሔር ሙላት ሁሉ ልክ ደርሰን እንሞላለን፤ ይህ ሙላት የሦስታንዱ አምላክ ብዙዎች የተካተቱበት መገለጥ የሆነችው ቤተ ክርስቲያን፣ የክርስቶስ አካል ናት—ቁ. 19።
8. የእግዚአብሔር ክብር ወደ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተሥርቷል፣ እርሱም ከምንለምነው እና ለምናስበው ሁሉ ይልቅ በቤተ ክርስቲያን በኩል ተገልጧል፤ በመሆኑም፣ እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ከብሯል—ቁ. 20-21።

ረ. ኤፌሶን 3፡16-21 የጳውሎስን መንፈስ፣ የውስጥ ፍላጎት፣ ጸሎት እና እምነት ያሳያል፡-

1. በመገለጥ የክርስቶስ ምሥጢር ለጳውሎስ ታውቋል (ቁ. 3-6)፤ ስለዚህ፣ መንፈሱ እና የውስጥ ፍላጉቱ—ያየው ነገር፣ የተናገረው ነገር፣ እና በልቡ ግድ የተሰኘለት ነገር—በውስጥ የሚያድረውን ክርስቶስ በውስጥ በመለማመድ በኩል እንደ የክርስቶስ አካል ከቤተ ክርስቲያን ግንባታ ራእይ ጋር የተገናኙ ነበሩ።
2. ጳውሎስ በዚህ ራእይ ተይዞ ነበር፣ ያም መንፈሱ እና የውስጥ ፍላጎቱ ሆነ፤ ስለዚህ፣ በኤፌሶን 3፡16-21 የተዘገበ እንዲህ ያለ ጸሎት ነበረው (በእምነት ክልል እና ንጥረ-ነገር)፤ በውስጥ የሚያድረውን ክርስቶስ በውስጥ በመለማመድ ክርስቶስ ቤተ ክርስቲያንን እንደ የክርስቶስ አካል እንዴት እንደሚገነባ ራእዩን ካየን፣ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔርን ስናገለግል የጳውሎስ መንፈስ፣ የውስጥ ፍላጎት፣ ጸሎት እና እምነት ይኖረናል።

*© 2021 Living Stream Ministry*